የከተሞች መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት የብድር አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 583/2013

Urban Drinking Water and Sanitation Service Provider Institutions and Irrigation Water User Associations Loan Disbursement Directive No. 583/2013

የውሃ ልማት ፈንድ
Water Resources Development Fund

ግንቦት 1፥ 2009

የከተሞች መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት የብድር አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 583/2013

የውሃ ልማት ፈንድ የብድር አሰጣጥና አወሳሰን መመዘኛዎችን በሕግ መምራት በማስፈለጉ፣ የፈንዱን የብድር አስተዳደር ሥርዓት ቀልጣፋና ለባለድርሻ አካላት ግልጽ ማድረግ በማስፈለጉ፣ የፈንዱን የብድር አሰጣጥ ሥርዓት ፍትሐዊ እና እኩል ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፣

የውሃ ልማት ፈንድን ለማቋቋምና አስተዳደሩን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 268/1994 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 7(2) እና 14(4) ለውሃ ልማት ፈንድ ቦርድ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ለከተሞች መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና ለመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት የብድር አሰጣጥን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 583/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1. "ጽ/ቤት" ማለት የውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት ነው።
2. "ብድር" ማለት ለከተሞች መጠጥ ውሀና ሳቴኒሽን ፕሮጀክቶችና ለመካከለኛና ከፍተኛ መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚውል ከጽ/ቤቱ በአነስተኛ ወለድ የሚሰጥ የረዥም ጊዜ ብድር ነው።
3. "ተበዳሪ ወይም ተበዳሪዎች" ማለት የከተማ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት ድርጅት/ድርጅቶች ወይም የመስኖ የህብረት ሥራ ማህበር/ማህበራት ነው።
4. "የሚመለከተዉ የክልል መንግሥት ማለት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግሥት ዕውቅና የተሰጣቸውን ዘጠኝ የክልል መስተዳድሮችን ሲሆን፣ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የአዲስ አበባንና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል።

Archive
Office of the Wa... Development Fund

5. “ፕሮጀክትን በትብብር ፋይናንስ ማድረግ” ማለት ለአንድ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚዉለዉን የብድር ፋይናንስ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ፋይናንሰሮች በትብብር መሸፈንና የፕሮጀክቱን ወጪ የመጋራት ስምምነት ነዉ።
6. “ዋና ዳይሬክተር” ማለት የጽ/ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ነው።
7. በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉ ሌሎች ቃላትና ሐረጐች የውሃ ልማት ፈንድን ለማቋቋምና አስተዳደሩን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 268/1994 (እንደተሻሻለ) የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።

3. የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በዚህ መመሪያ ትርጓሜ ክፍል አንቀጽ 2(3) በተመለከቱ ተበዳሪዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

4. የመመሪያው ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዋና ዓላማ የውሃ ልማት ፈንድን የብድር አስተዳደር ሥርዓት ወጥነት ያለው፣ ግልጽ እና ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ ሲሆን፣ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል።

1. ብቁ ለሆኑ ተበዳሪዎች የሚሰጠው ብድር አመዳደብ ፍትሃዊ መሆኑን ማረጋገጥ፣
2. ለተበዳሪዎች የሚሰጠው የብድር አገልግሎት ጥራት ያለው፣ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ እና
3. የተበዳሪዎችን የሥራ አፈፃፀም፣ የሂሳብና ንብረት አያያዝ መቆጣጠር እንዲቻል ማድረግ ፣

ነው።

ክፍል ሁለት
የብድር አሰጣጥ ሥርዓት

5. የሚሰጠው የብድር አይነት

1. ጽ/ቤቱ ለተበዳሪዎች የእፎይታ ጊዜውን ጨምሮ ቢያንስ ከ15(አሥራ አምስት ዓመት) እስከ 30(ሠላሳ) ዓመት ተከፍሎ የሚያልቅ የረጅም ጊዜ ብድር ይሰጣል።
2. ብድሩ በዋነኝነት የሚሰጠው ተበዳሪዎች ለሚያከናውኗቸው ለከተማ ውሃ አቅርቦት እና ሳኒቴሽን ፕሮጀክቶች እንዲሁም ለመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች አዳዲስ ግንባታዎች እና ዋና ዋና የማስፋፊያ ሥራዎች ዓላማ ነው።

6. የብድር አሰጣጥ ሂደት

የብድር አሰጣጥ ሂደት ከተበዳሪዎች የብድር ማመልከቻ ከመቀበል ጀምሮ ብድሩን እስከ መሰብሰብ ያሉትን ደረጃዎች የሚያካትት ነው።

Archives
Office of the Water Resources Development Fund

1. **የብድር ማመልከቻ**

ሀ. ከፈንዱ ለመበደር ብቃት ያለው ማናቸውም ተበዳሪ በጽ/ቤቱ የተዘጋጀውን የብድር ማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ለጽ/ቤቱ ማቅረብ አለበት።

ለ. በጽ/ቤቱ የሚዘጋጀው የብድር ማመልከቻ ቅጽ የተበዳሪውን ማንነት፣ የፕሮጀክቱን ዓይነት እና የብድሩን መጠን በግልጽና በተብራራ ሁኔታ ለመረዳት የሚያስችል መሆን አለበት።

2. **የብድር ማመልከቻ ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑ ሠነዶች**

ማናቸውም ተበዳሪ ከብድር ማመልከቻው ቅጽ ጋር በማያያዝ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሰነዶችን እንደ አግባብነቱ ማቅረብ አለበት፣

ሀ. ፕሮጀክቱ ወጪ ቆጣቢ፣ አስተማማኝ እና ተገቢ መሆኑን የሚያረጋግጥ ደረጃውን የጠበቀና በቅርብ ጊዜ የተዘጋጀ የፕሮጀክት የአዋጭነት ጥናት ሰነድ፣ ዝርዝር ዲዛይን፣ የጨረታ ሰነድ እና ቢዝነስ ፕላን፣

ለ. ተቋሙ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ስለመሆኑ በሕግ ስልጣን ባለው አካል የተሰጠ ማረጋገጫ፣

ሐ. የተቋሙ የምዝገባ ሰነድ፣ ፈቃድ ወይም የመመስረቻ ጽሁፍ፣

መ. ተቋሙ ብድር ለመጠየቅና ለመበደር የሚችል መሆኑን የሚያረጋግጥ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የውክልና ሥልጣን ማስረጃ፣

ሠ. በሥራ ላይ ያለው የተቋሙ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ስም ዝርዝር የያዘ፣ ቦርዱ የተቋቋመበት እና ባለድርሻዎቹ ለቦርዱ የውክልና ሥልጣን የሰጡ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ፣

ረ. ተቋሙ የሚበደረውን ገንዘብ ለመክፈል የሚያስችል በቂ የፋይናንስ አቅም ወይም ችሎታ ያለዉ ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ፣ እና

ሰ. ብቁ እና አስተማማኝ የሆነ ከሚመለከተው የክልል መንግሥት የተሰጠ የዋስትና ማረጋገጫ ሰነድ ፣

ናቸው።

3. ጽ/ቤቱ ተበዳሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የሚያቀርባቸውን ሰነዶች በመመርመር ተበዳሪው ለብድሩ ብቁ መሆኑን መመዘን አለበት።

7. የፕሮጀክት አዋጭነት ግምገማ

1. ጽ/ቤቱ ብድሩን ከማጽደቁ በፊት ደረጃቸውን በጠበቁ የግምገማ መስፈርቶች እና መመዘኛዎች በመጠቀም ጠንካራ እና ጥልቀት ያለው የፕሮጀክት አዋጭነት ግምገማ ማድረግ አለበት።

መዝገብ ቤት Archives Office of the ...

2. ጽ/ቤቱ የአዋጭነት ግምገማዉን ሲያከናውን የፕሮጀክቱን የቴክኒክ ብቃት፣ የፕሮጀክቱን የፋይናንስ አዋጭነትና አስተማማኝነት፣ፕሮጀክቱ ለህብረተሰቡ የሚሰጠው ማህበራዊ ጠቀሜታ፣ተቋሙ ሊያሰራ የሚያስችል ተቋማዊ አደረጃጀትና አስተዳደራዊ ብቃት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

3. የአካባቢና የማህበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ ሥርዓት ያለፈ መሆን ይኖርበታል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ጽ/ቤቱ በሚከተለው የአሠራር ቅደም ተከተል መሠረት የፕሮጀክት ግምገማውን ማከናወን አለበት፡፡

   ሀ. ብድር ለማግኘት መሟላት የሚጠበቅባቸውን የመመዘኛ መስፈርቶች ለአመልካች ተበዳሪው በዝርዝር ያስረዳል፣
   ለ. የመመዘኛውን መስፈርት ዝርዝር የያዘ ሰነድ እና የማመልከቻ ቅጹን ለአመልካች ተበዳሪው ይሰጣል፣
   ሐ. አመልካች ተበዳሪው በአንቀጽ 6(2) መሠረት የሚያቀርባቸውን ሰነዶች በመመርመር ይተነትናል፣
   መ. ፕሮጀክቱን በአካል ተገኝቶ በመጎብኘት ተበዳሪ አመልካቹ ካቀረበው ሰነድ ጋር ትክክለኛነቱን በማመሳከር የተበዳሪውን አቅም ይመዝናል፣
   ሠ. የፕሮጀክት አዋጭነት ግምገማና ትንተና ሪፖርት በማዘጋጀት ያጠናክራል፣
   ረ. የተዘጋጀውን የመጨረሻ የግምገማ ሪፖርት ለዋና ዳይሬክተሩ ያቀርባል፣
   ሰ. ሪፖርቱ በዋና ዳይሬክተሩ ይሁንታ ሲያገኝ ብድሩ እንዲፀድቅ ሪፖርቱን ለቦርዱ ውሳኔ ያቀርባል፡፡
   ሸ. የቦርዱን ውሳኔ መሠረት በማድረግ ጽ/ቤቱ የብድሩ ጥያቄ ተቀባይነት ማግኘቱን ወይም ተጨማሪ ማሻሻያ የሚያስፈልገው መሆኑን ወይም ተቀባይነት ያላገኘ መሆኑን ለአመልካች ተበዳሪው በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

8. <u>የብድር አፈቃቀድ</u>

1. ጽ/ቤቱ ብድሩን ለማፅደቅ ለቦርዱ በሚያቀርበው የፕሮጀክት አዋጭነት ግምገማ ውጤት ላይ በቦርዱ በሚነሱና ማብራሪያ በሚሹ ጥያቄዎች ላይ የጽ/ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ቦርዱ በሚያደረገው ስብሰባ ላይ በመገኘት አስፈላጊውን ገለጻ ማድረግ አለበት፡፡
2. በአመልካች ተበዳሪው የሚቀርበውን የብድር ጥያቄ የማጽደቅም ሆነ የመሰረዝ ሙሉ ስልጣን ያለው ቦርዱ ነው፡፡

9. <u>የብድር ድርድር እና ስምምነት</u>

1. ብድሩ በቦርዱ ሲፀድቅ በጽ/ቤቱ እና በተበዳሪው መካከል የተዋዋይ ወገኖችን ፍላጎትና ጥቅም ለመጠበቅ የሚያስችል የብድር ስምምነት ድርድር መደረግ አለበት፡፡

መዝገብ ቤት
Archives
Office of the W...

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1መሠረት በሚደረገው ድርድር ስምምነት ላይ የተደረሰ እንደሆነ በጽ/ቤቱ ዋና ዳይሬክተር እና በተበዳሪው ወይም ተበዳሪው ሕጋዊ ውክልና በሰጠው ኃላፊ መካከል የብድር ውል ስምምነት ይከናወናል፡፡

3. የብድር ውል ስምምነቱ በጽ/ቤቱ ፋይናንስ በሚደረጉ የፕሮጀክቶች ዝርዝር ውስጥ መመዝገብ አለበት፡፡

ክፍል ሦስት
ዋና ዋና የብድር ሁኔታዎች እና ግዴታዎች

10. የብድር አጠቃላይ ሁኔታዎችና ግዴታዎች

1. ጽ/ቤቱ ከተበዳሪዎች ጋር የሚገባው የብድር ስምምነት ዉል ከዚህ በታች ከአንቀጽ11 ጀምሮ በዝርዝር በተቀመጡት ደረጃቸውን የጠበቁ የብድር ሁኔታዎችና ግዴታዎች ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡

2. እነዚህ ዋና ዋና የብድር ሁኔታዎችና ግዴታዎች የብድር ስምምነቱ አጠቃላይ ክፍል አንድ አካል ናቸው፡፡

11. የብድር መጠን

ጽ/ቤቱ ሊሰጥ የሚችለው ከፍተኛ የብድር መጠን የሚወሰነው በፕሮጀክቱ አዋጭነት ግምገማ ውጤት፣ በቦርዱ የውሣኔ ሀሳብ እና ጽ/ቤቱ ሊመድበው ከሚችለው የፈንድ አቅርቦት መጠን ጋር የተገናዘበ መሆን ያለበት ሲሆን፣ በማናቸውም ሁኔታ ከፕሮጀክቱ አጠቃላይ ወጪ ግምት 80% (ሰማኒያ በመቶ) በላይ ሊሆን አይችልም፡፡

12. የወለድ መጣኔ

የውጭ አበዳሪ ተቋማት ወለድን በሚመለከት የሚያስቀምጡት ቅድመ ሁኔታ ከሌለ ቦርዱ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ከሚወስነው ጣሪያ ሳያልፍ ጽ/ቤቱ ለተበዳሪዎች በሚሰጠው ብድር ላይ የሚከፈለውን የወለድ መጠን ይወስናል፡፡

13. የእፎይታ ጊዜ

1. ጽ/ቤቱ የብድር መመለሻ ጊዜውን መሠረት በማድረግ እና እንደ ፕሮጀክቱ ስፋትና ደረጃ በመመዘን የብድሩን የእፎይታ ጊዜ መወሰን ያለበት ሲሆን፣ በማናቸውም ሁኔታ የእፎይታ ጊዜው ከአምስት ዓመት በላይ ሊሆን አይችልም፡፡

መዝገብ ቤት
Archives
Office of the Water Resources Development Fund

2. የእፎይታ ጊዜው የሚቆጠረው ከብድሩ ገንዘብ ላይ የመጀመሪያዉ ክፍያ ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ ነው።
3. የሚሰራው ፕሮጀክት በተለያዩ ምክንያቶች በማናቸውም ደረጃ ላይ እያለ ያልተጠናቀቀ መሆኑ ጽ/ቤቱ የእፎይታ ጊዜዉ እንደተጠናቀቀ ያለውን ብድር የማስመለስ መብቱን አያስቀርም።

14. የብድር መክፈያ ጊዜ

1. ጽ/ቤቱ በሚያደርገው የብድር ስምምነት የብድር መክፈያ ጊዜውን ከዚህ በላይ በአንቀጽ 5(1) በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሠረት መወሰን ያለበት ሲሆን፣ አወሳሰኑ የፕሮጀክቱን የኢንቨስትመንት ስፋት፣ ከውጭ አበዳሪ ወይም ለጋሽ ተቋሙ ጋር በተደረገው ስምምነት የተቀመጠው የብድር መክፈያ ጊዜ እና የተበዳሪውን የመክፈል አቅም ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት።
2. ከዚህ በላይ በአንቀጽ 5(1) የተደነገገው የጊዜ ገደብ ቢኖርም ጽ/ቤቱ የፕሮጀክቱ ወጪ ከፍተኛ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ እና ተበዳሪው ብድሩን በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ከፍሎ ለመጨረስ የሚያስችል አቅም የሌለው መሆኑ በአዋጭነት ግምገማው ተረጋግጦ ሲቀርብለት በተለየ ሁኔታ የብድር መክፈያ ጊዜውን ሊያሻሽለው ይችላል።
3. ተበዳሪው በብድር ስምምነቱ መሰረት ስምምነት ላይ በተደረሰበት የጊዜ ገደብ ውስጥ አሳማኝ በሆነ ምክንያት ብድሩን መክፈል ያልቻለ እንደሆነ የብድሩ መክፈያ ጊዜ እንዲራዘምለት ጥያቄውን በጽሑፍ ለጽ/ቤቱ ማቅረብ ይችላል።
4. ፅ/ቤቱ በተበዳሪው የቀረበው ምክንያት አሳማኝና ተቀባይነት ያለው ሆኖ ሲያገኘው የብድሩ መክፈያ ጊዜ ለአንድ ጊዜ ብቻ ከአምስት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ እንዲራዘም ለቦርዱ አቅርቦ ያስጸድቃል።

15. የብድር አከፋፈል ዑደት

ማናቸውም ተበዳሪ በዓመት ሁለት ጊዜ በሚፈፀም እኩል ክፍያ የብድሩን ገንዘብ መመለስ አለበት።

16. ቅጣት

1. ተበዳሪው በብድር ስምምነቱ መሠረት ያለበትን ማናቸውንም ግዴታ ያልፈፀመ እንደሆነ በብድር ስምምነቱ የተወሰነውን ዓመታዊ የወለድ መጠን 1/3 ከወለድ በተጨማሪ በቅጣት መልክ ይከፍላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እና ጽ/ቤቱ ለብድሩ መመለስ የሚያደርጋቸው ተጨማሪ የክትትልና ድጋፍ ሥራዎች እንደተጠበቁ ሆነው ተበዳሪው በብድር ስምምነቱ መሠረት ሁለት ተከታታይ ክፍያዎችን (Two consecutive semi-annual installments) ያልፈፀመ እንደሆነ ጽ/ቤቱ ጉዳዩን አግባብ ላለው የሕግ አካል በማቅረብ እልባት እንዲያገኝ ማድረግ አለበት።

ማት ፈንድ ጽ/ቤት
መዝገብ ቤት
Archives
Office of the Water Resources Development Fund

17. የብድር ዋስትና

1. ተበዳሪው ከጽ/ቤቱ ለወሰደው ብድር መመለስ ከሚመለከተው የክልል መንግሥት ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት የብድር ዋስትና ማረጋገጫ ደብዳቤ የብድር ስምምነቱ ከመፈረሙ በፊት ማቅረብ አለበት፡፡
2. ተበዳሪው ብድሩን በብድር ስምምነቱ መሠረት የብድር መክፈያ ጊዜው ሲደርስ አስቀድሞ በጀት በማስያዝ ብድሩን በወቅቱ መክፈል የሚችል መሆኑን የሚገልጽ የዋስትና ማረጋገጫ ደብዳቤ ከሚመለከተው የከተማ አስተዳደር የብድር ስምምነቱ ከመፈረሙ በፊት ማቅረብ አለበት፡፡

18. በብድር ውል መሠረት አለመፈፀም

ተበዳሪው በብድር ስምምነቱ መሰረት ያለበትን ማናቸውንም ግዴታ ያላከበረ እንደሆነ የውል ጥሰት እንደፈፀመ የሚቆጠር ሲሆን፣ በዋነኛነት የሚከተሉትን ይጨምራል፡፡

ሀ. ተበዳሪው ዋናውን የብድር ገንዘብ ወይም ወለዱን በብድር ስምምነቱ የጊዜ መክፈያ ሰሌዳ መሠረት ያልከፈለ እንደሆነ፣

ለ. ከጽ/ቤቱ እውቅና እና ፈቃድ ውጭ ከሌላ የገንዘብ ተቋም ጋር የብድር ስምምነት ያደረገ እንደሆነ፣

ሐ. ከጽ/ቤቱ እውቅና ውጭ በፕሮጀክቱ አፈፃፀም ላይ ጉልህ የሆነ አሉታዊ ለውጥ ያደረገ እንደሆነ፣

ነው፡፡

19. ተጨማሪ ብድር

1. ጽ/ቤቱ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች በልዩ ሁኔታ ተጨማሪ ብድር ሊፈቅድ ይችላል፡፡

   ሀ. ተበዳሪው በፕሮጀክቱ የመጀመሪያ የግንባታ ዕቅድ መሠረት ፕሮጀክቱን ለማጠናቀቅ የበጀት ዕጥረት ያጋጠመው እንደሆነ፣

   ለ. የፕሮጀክቱን የልማት ውጤታማነትና ሊያመጣ የሚችለውን አዎንታዊ አስተዋጽኦ ለማሻሻል የሚረዱ ተጨማሪ ሥራዎች ለማከናወን የሚያስችል ተጨማሪ ገንዘብ መመደብ አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ፣

   ሐ. የፕሮጀክቱ ተግባር እና አሠራር መዋቅራዊ ለውጥ ሲደረግበትና በለውጡ የተነሳ ቀደም ሲል የተወሰደው የብድር ገንዘብ አዲሱን የፕሮጀክት ሥራ ለማከናወን በቂ ሆኖ ያልተገኘ እንደሆነ ፣

   ነው፡፡

...ማት ፈንድ ጽ/ቤት
መዝገብ ቤት
Archives
Office of the Water Resources Development Fund

2. ጽ/ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ የተጠቀሱት ምክንያቶች አሳማኝና ተቀባይነት ያላቸው መሆኑን አረጋግጦ ተጨማሪ ብድር ሊሰጥ የሚችለው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው፡፡

ሀ. የፕሮጀክቱ የግንባታ ሂደት በብድር ስምምነቱ መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ የተፈፀመ ሲሆን፣

ለ. የተጨማሪ ብድሩ ጥያቄው በፕሮጀክት አዋጭነት ግምገማ መመዘኛዎች ተፈትሾተቀባይነቱ የተረጋገጠ ሲሆን እና

ሐ. ተጨማሪ ብድሩ በመጀመሪያው ታሪፍ ላይና በተበዳሪው የመክፈል አቅም ላይ ጉልህ የሆነ አሉታዊ ተጽህኖ የሌለው እንደሆነ፣

ነው፡፡

3. ጽ/ቤቱ በሚሰጠው ተጨማሪ ብድር ላይ የሚከፈለው የወለድ መጠን ለዋናው ብድር ከሚከፈለው የወለድ መጠን ጋር ተመሣሣይ ነው፡፡
4. ጽ/ቤቱ ተጨማሪ ብድሩን ከመፍቀዱ በፊት አዋጭነቱን ገምግሞ በቦርዱ ማስጸደቅ አለበት፡፡
5. ጽ/ቤቱ የዋናውን ብድር የመክፈያ የጊዜ ሰሌዳ ሳይለውጥ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ጊዜውን በማራዘም ተጨማሪውን ብድር ሊሰጥ ይችላል፡፡ ሆኖም በማናቸውም ሁኔታ ለተጨማሪው ብድር ጽ/ቤቱ አዲስ የብድር አከፋፈል ጊዜ ሰሌዳ (Amortization schedule) ማዘጋጀት አለበት፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው ቢኖርም ጽ/ቤቱ የፈንድ ዕጥረት ያጋጠመው እንደሆነ ተጨማሪ ብድር ለመስጠት አይገደድም፡፡

20. <u>የፕሮጀክት ወጪ መጋራት</u>

1. ተበዳሪው በፕሮጀክት ወጪ መጋራት መርህ መሠረት የሚፈለግበትን የፕሮጀክት መዋጮ ገንዘብ ስምምነት ላይ በተደረሰበት ጊዜ ሠሌዳ መሠረት ገቢ ማድረግ አለበት፡፡
2. ተበዳሪው የሚያዋጣዉን የፕሮጀክት መዋጮ ገንዘብ መጠንና ገንዘቡ ወደ ጽ/ቤቱ ባንክ ሂሣብ መተላለፍ ያለበትን ጊዜ በተመለከተ አስቀድሞ በጽ/ቤቱ እና በተበዳሪው መካከል በሚደረግ ስምምነት መሠረት የሚወሰን ይሆናል፡፡ ሆኖም በማናቸውም ሁኔታ የፕሮጀክቱን የትግበራና የክፍያ ጊዜ ሰሌዳ መሠረት በማድረግ ከተበዳሪው የሚፈለገው የፕሮጀክት መዋጮ ገንዘብ በየበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ወደ ጽ/ቤቱ ባንክ ሂሣብ ገቢ መደረግ አለበት፡፡
3. ጽ/ቤቱ የብድሩን ገንዘብ ለክፍያ መልቀቅ የሚችለው ተበዳሪው ስምምነት ላይ በተደረሰበት ጊዜ ሠሌዳ መሠረት የሚፈለግበትን የፕሮጀክት መዋጮ ገንዘብ ለጽ/ቤቱ ገቢ ማድረጉን ሲያረጋግጥ ብቻ ነው፡፡

Archives
Office of the Water Resources Development

21. የብድሩ ገንዘብ የሚለቀቅበት ዘዴ

1. ጽ/ቤቱ የካሽ ፍሎው የክፍያ አፈፃፀም ዘዴን በመጠቀም የብድሩን ገንዘብ ለክፍያ መልቀቅ አለበት፣
2. ክፍያው የሚፈፀመው ተበዳሪው ከሦስት እስከ ስድስት ወራት ያህል የሚኖረውን የክፍያ ዕቅድ ከተፈረመ የውል ሰነድ እና የወጪ ሪፖርት ጋር አያይዞ ለጽ/ቤቱ ሲያቀርብ ነው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው ቢኖርም ጽ/ቤቱ ከተበዳሪው ወይም ከፕሮጀክቱ አስፈፃሚ አካል ጥያቄ ሲቀርብለትና ሁኔታዎች አስገዳጅ በሚሆኑበት ጊዜ እንዲሁም አስፈላጊነቱ ሲያምንበት ክፍያውን በቀጥታ ለባለመብቶቹ ሊከፍል ይችላል፡፡

22. የግዥ አፈፃፀም ሥርዓት

1. ተበዳሪው በብድር ስምምነቱ መሠረት በብድሩ ገንዘብ የማናቸውንም የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ የሚያከናውነው ግልጽ በሆነ አሠራር እና በግዥ አፈፃፀም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘቱን በማረጋገጥ ነው፡፡
2. በብድር ስምምነቱ መሠረት በብድሩ ገንዘብ ማናቸውንም ግዥዎች በኃላፊነት የሚያስፈጽመው ተበዳሪው ወይም የፕሮጀክቱ አስፈፃሚ አካል ነው፡፡
3. ተበዳሪው ማንኛውንም የፕሮጀክት የግንባታ ዕቃ ወይም አገልግሎት ግዥ ከመፈፀሙ በፊት በቅድሚያ ለጽ/ቤቱ አቅርቦ ይሁንታ ማግኘት አለበት፡፡
4. ጽ/ቤቱ ለግዥው ይሁንታ ሊሰጥና ከብድሩ ገንዘብ ላይ የግዥ ክፍያ በሙሉም ሆነ በከፊል ሊለቅ የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው፡፡

   ሀ. ተበዳሪው የሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት ጥራት ከሚከፈለው ዋጋ ጋር ተመጣጣኝ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

   ለ. የውጭ አበዳሪ ወይም የለጋሽ ተቋሙን ደንብና መመሪያ የተከተለ ግዥ ስለመሆኑ ይሁንታ (No-objection) ማግኘቱ ሲረጋገጥ፣

   ሐ. ግዥው የሚፈጸመው ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ገንዘብ ከሆነ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት የግዥ አዋጅና መመሪያን ተከትሎ የተፈፀመ ስለመሆኑ የጽ/ቤቱን ይሁንታ ያገኘ መሆኑን ሲረጋገጥ እና

   መ. የተበዳሪውን የሂሣብ ሰነዶችን ትክክለኛነት እና ቀደም ሲል ተለቆ የነበረው የብድር ገንዘብ በአግባቡ በሥራ ላይ መዋሉን ሲያረጋግጥ

   ነው፡፡

መዛግብት ቤት Archives Office of the Water Resources Development Fund

23. <u>የሂሣብና ሌሎች ሰነዶች አያያዝ</u>

1. ጽ/ቤቱ የሰጠውን ብድር በአግባቡ ለማስተዳደር እና ለመቆጣጠር የሚያስችለውን የፋይናንስ እንቅስቃሴውን የሚያሳይ አስተማማኝ የሂሣብ ምዝገባ ዘዴ መከተል አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ጽ/ቤቱ ያልተከፈለ ቀሪ ብድርን፣ጊዜው ያለፈበት ዕዳ እና ተመሳሳይ ሁኔታዎችን ለመከታተል የሚያስችለውን ሌሎች እንደ ማስታወሻ የሚረዱ የመመዝገቢያ ዘዴዎችን ሊጠቀም ይችላል፡፡
3. ጽ/ቤቱ ጤናማ ያልሆኑ ዕዳዎችን እና ሥራዎችን በመከታተል ወቅታዊ የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድና ፈንዱን ከኪሣራ ለማዳን የሚያስችለውን የተለየ የሂሳብና የክትትል ሥርዓት መዘርጋት አለበት፡፡
4. ተበዳሪው ጽ/ቤቱ የሂሣብ እንቅስቃሴውን ለመቆጣጠርና የብድሩን ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ ማዋሉን ለማረጋገጥ እና ለመከታተል የሚያስችለውን የራሱን የሂሳብና ሌሎች ሰነዶች የምዝገባ ዘዴ መከተል አለበት፡፡
5. ተበዳሪው እያንዳንዱን የፕሮጀክቱን ቋሚ ንብረት እና ስቶክ በዋጋና በብዛት ለይቶ በቋሚ ንብረት መዝገብ እና በስቶክ ካርድ እንደቅደም ተከተላቸው እንዲሁም የቋሚ ንብረቶችን ዋጋ በዋናው ሌጀር ላይ መመዝገብ አለበት፡፡

24. <u>የሂሣብ እና ኦዲት ሪፖርት</u>

1. ተበዳሪው የጽ/ቤቱን የሂሣብ ሪፖርት ቅጽ በመጠቀም የፕሮጀክቱን ወርሃዊ ፣ የሦስት ወርና ዓመታዊ የሂሣብ ሪፖርት በየጊዜው ለጽ/ቤቱ ማቅረብ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተበዳሪዉ ፕሮጀክቱ በግንባታ ላይ እስካለ ድረስ የዓመቱን የሂሣብ ኦዲት ሪፖርት የፌዴራሉ መንግስት በጀት ዓመት እንደተጠናቀቀ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ለጽ/ቤቱ አጠናክሮ ማቅረብ አለበት፡፡

<u>ክፍል አራት</u>
<u>የብድር ፈንድ ድልድልን እንደገና ስለማሻሻል</u>

25. <u>መርህ፣</u>

1. ጽ/ቤቱ የፕሮጀክቱን የአፈፃፀም ሂደት ወይም የታለመለትን ዓላማ ሳይለውጥ የብድር ፈንዱን በራሱ ወይም በውጭ አበዳሪ ወይም ለጋሽ ተቋሙ በሚያስቀምጠው ቅድመ ሁኔታ መሰረት እንደገና ሊደለድል ይችላል፡፡

መዝገብ ቤት
Archives
Office of the Water Resources Development Fund

2. ጽ/ቤቱ የብድር ፈንዱን እንደገና ሊደለድል የሚችለው በፕሮጀክቱ የወጪ አርስቶች እና በፕሮጀክቱ ተመሳሳይ የወጪ አርዕስት መካከል ሆኖ የፕሮጀክቱን ቀሪ የብድር ገንዘብ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

26. በፕሮጀክቱ የወጪ አርዕስቶች መካከል የሚደረግ የፈንድ ዝውውር

1. ተበዳሪው በማንኛውም የፕሮጀክቱ የወጪ አርዕስት ሥር የተመደበው ፈንድ በቂ ያልሆነ እንደሆነ በፕሮጀክቱ የወጪ አርዕስቶች መካከል የፈንድ ዝውውር እንዲደረግ ጥያቄውን ለጽ/ቤቱ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ጽ/ቤቱ በተበዳሪው የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ሲያገኘው ተጨማሪ ፈንድ መመደብ ሳያስፈልገው ተበዳሪው በሚያቀርበው አማራጭ መሠረት ከአንዱ የወጪ አርዕስት ላይ ቀንሶ ዕጥረት ወዳለበት ወደ ሌላኛው የፕሮጀክቱ የወጪ አርዕስት ማዛወር ይችላል፡፡

27. በተመሳሳይ የወጪ አርዕስት መካከል የሚደረግ የፈንድ ዝውውር

1. ተበዳሪው በተመሳሳይ የወጪ አርዕስት መካከል የፈንድ ዝውውር ለማድረግ ጥያቄውን ለጽ/ቤቱ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ጽ/ቤቱ በተበዳሪው የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ሲያገኘው ተበዳሪው ዝውውሩን እንዲያደርግ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

28. የፕሮጀክት ቀሪ የብድር ገንዘብ አጠቃቀም

ጽ/ቤቱ በተበዳሪው ጥያቄ አቅራቢነት የፕሮጀክቱ ግንባታ ከተጠናቀቀ በኋላ ለፕሮጀክቱ ሥራ ተመድቦ በጥቅም ላይ ሳይውል የቀረውን ተራፊ የብድር ገንዘብ ከተበዳሪው ጋር በሚያደርገው የብድር ማሻሻያ ስምምነት መሠረት ገንዘቡ ለማናቸውም የፕሮጀክቱ የወጪ አርዕስቶች እንደገና ተደልድሎ ጥቅም ላይ እንዲውል ሊፈቅድ ይችላል፡፡

ክፍል አምስት
ፕሮጀክትን በትብብር ፋይናንስ ስለማድረግ

29. በትብብር ፋይናንስ ስለማድረግ

1. አዋጭነቱ ተገምግሞ ብቁ የሆነ ፕሮጀክት ሆኖ ነገር ግን ለፕሮጀክቱ ማስፈፀሚያ የሚያስፈልገው ገንዘብ ከፍተኛ ሆኖ የተገኘ ከሆነ ፕሮጀክቱን ጽ/ቤቱ ከሌላ

የውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት
መዝገብ ቤት
Archives
Office of the Water Resources Development Fund

የፋይናንስ ተቋም ጋር በሚያደርገው የብድር ፈንድ መጋራት ስምምነት መሠረት ፋይናንስ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2. በዚህ የፕሮጀክት ፋይናንሲንግ ስምምነት በዋነኝነት የውጭ ፋይናንሰሮች፣ የፌዴራል መንግስት፣ የክልል መንግስት እና የከተሞች የመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን አገልግሎት ተቋማት የፕሮጀክቱ ፋይናንስ ምንጮችና ተባባሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ክፍል ስድስት
የብድር ፈንድ አመዳደብ መሠረታዊ ሥርዓት

30. የብድር ጥሪ

ጽ/ቤቱ በብድር ፋይናንስ ሊሆኑ የሚችሉ ፕሮጀክቶች በሚወስነው ጊዜ ገደብ መሠረት እንዲቀርቡለት ለሁሉም ክልሎች በተመሳሳይ ጊዜ ጥሪ ማስተላለፍ አለበት፡፡

31. ፍትሐዊነት እና እኩል ተጠቃሚነት

1. ጽ/ቤቱ ለብድር ብቁ የሆኑ ተበዳሪዎችን የማጣራት ተግባሩን ሲያከናውን የክልሎችን ፍትሐዊና እኩል ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

2. ጽ/ቤቱ ከውጭ ፋይናንስ የሚያፈላልግላቸውን ፕሮጀክቶች ዝርዝር ለውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ወይም ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ከማስተላለፉ በፊት የሚመረጡት ፕሮጀክቶች የክልሎችን ፍትሐዊና እኩል ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ ተግባራዊ እንዲሆኑማድረግ አለበት፡፡

ክፍል ሰባት
ልዩ ልዩ

32. መመሪያውን ስለማሻሻል

ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

Archives
Office of the Water Resources Development Fund

33. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከግንቦት 7 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ግንቦት 7 .... ቀን 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አቶ ከበደ ገርባ

የውሀ ልማት ፈንድ ቦርድ ሰብሳቢ